# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)


ነሐሴ 15 ቀን 2002 ዓ.ም.

### መለስ ዜናዊ ሞተ ቀጥሎስ ?

በአንድ ሀገርና ሕዝብ ታሪክ ሂደት ብቅ የሚሉ አምባገነን መሪዎች ሚናቸው ከባድ ሆኖ መገኘቱ የሚጠበቅ
ነው፡፡ አምባገነኑ በሀገርና ሕዝብ የዴሞክራሲ ፍላጎት ላይ ደንቃራ ሆኖ ሲመጣና የስልጣን ባለቤትነቱም ፍ
ፁም ሆኖ ሲገኝ ግለሰቡን በማስወገድ ላይ ያተኮረ ጥረትናትግል መካሄዱ የግድ ይሆናል፡፡ ፋሺስቱ ደርግ ስ
ልጣን እንደያዘ  አምባገነን ሆኖ የመጣውን  መንግሥቱ ኃይለማርያምን ከመድረክ ለማስወገድ ኢሕአፓ ያ
ደረጋቸው ጥረቶች የሚታወሱ ናቸው ፡፡

መለሰ ዜናዊ ኢትዮጵያና ሕዝቧን የሚጠላ ፤ ሥልጣንን በግሉ ቁጥጥር ያስገባ ጨካኝና አረመኔ አምባገነን እ
ንደ ነበር ከደጋፊዎቹ በስተቀር  ሌላው ሕዝብ የሚያውቀው ሀቅ ነው፡፡ ስለዚህም ሞቱ ያለው የፖለቲካ አን
ደምታ በቀላሉ የሚገመት ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ አንደምታ ለሕዝብ በሚበጅ መንገድ  ቃናው ይከሰታል
ወይም ይደመጣል የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ ፍፁም ሥልጣንን ጨብጦ የነበረው ግብዝ በመሞቱ በቅድ
ሚያ በቀውስ ሲናጥ የባጀው ወያኔ ወደ ባሰ ሹክቻ መግባቱ የሚጠበቅ ነው፡፡ ይህ ክስተት ደግሞ በአጠቃላይ
ለሕዝብ ይበጃል--ወያኔ ይዳከማል፥ ይበጣበጣል- ማለት ቢቻልም የወያኔ ወድቀት ያመጣል ብሎ መደም
ደም አሁን የሚቻል አይደለም ፡፡ መለስ ዜናዊ የግል መጋዣ ሆኖ ያገለጋላቸውና ኢትዮጵያን የሸጠላቸው
ባዕዳን ሁሉ በመሞቱ ማዘናቸው የሚጠበቅ ሲሆን መለስን በሌለ መሰል ቡቸላ ለመተካት ደግሞ መራወጥ ከ
ጀመሩ ጊዜ ማለፉን አንስተውም ፡፡ መለስ በምዕራባውያን ተላለኪነት በአፍሪቃ--በተለይም በአፍሪቃ ቀንድ
--የነበረው ሚና ሰፊ ነበርና ሞቱ ቢያንስ በአፍሪቃ ቀንድ የማይናቅ አንደምታ ሊኖረው እንደሚችልም መ
ጠበቅ ይቻላል፡፡ ይህም ዕይታን ፤ክትትልንና ትኩረትንም የሚጠይቅ ጉዳይ ይሆናል፡፡

የመለስን ሞት ለጥቅማቸው ለማዋል ባዕዳን እንደሚጥሩት ሁሉ ሀገር ወዳዶችም ይህ ሊፈጥረው የሚችለው
ን ክፍተት ተገንዝበው ሕዝባዊ ግባቸውን ለማሳካት መዋደቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምዕራባውያን በተለይም አ
ሜሪካ መለስ ቢሞትም በሌላ ወያኔ ተክተውና የወያኔን አገዛዝ መሰረቱንና ይዘቱን ጠብቀው፤ አዲስ ተመሳ
ሳይ ጭምብል አጥልቀውለት፤ በለማዱ ቅጥረኞች አጅበውት የመለስን ስርዓት ለመቀጠል ተነስተዋል ፡፡ ከቅ
ርብ ጊዜ ወዲህ ይህን የባዕድ ተልዕኮ ከግብ ለማድረስ ደፋ ቀና የሚሉትን ቅጥረኞች በሞላ ስንታዘብ ቆይተ
ናል ፤ እየታዘብንም ነው፡፡ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችንም ለባዕድ ስላልሰገዱ አክራሪ በሚል ለማግለል ስራው


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ተጧጡፏል ፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ከተጠበቀ ሀገራችን የባዕድ መፈንጪያና መጫወቻ አትሆንምና ባዕዳን የመለስ ሞት ውድቀታቸውንና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እንዳያበስር ባላቸው አቅም ሁሉ እየጣሩ ና ቸው ፡፡ ይህን ጥረት የሚደግፉ ግን ተቃዋሚ ነን የሚሉ ድርጅቶች እንዳሉ ደግሞ ምስጢር አይደለም ፡፡ በ ኢሕአፓ ግምገማ በወያኔ አመራርውስጥ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም የሚያስቀድሙና የዘረኛውን ስርዓት ሂደትና እርምጃ ሁሉ የሚቃወሙ የሉም፡፡ ከወያኔዎች ዴሞክራሲያዊ ሽግግርን መጠበቅ ከእባብ ዕንቁላል ርግብ ትወለዳለች ብሎ መመኘት ነው ፡፡ ምን ያህል ተለጣፊዎች ሌላ ቢመኙ ቢለፍፉ ዴሞክራሲያዊ ሽግ ግርና ወያኔያዊ አገዛዝ/ስርዓት ተፃራሪ ናቸው ፡፡ ወያኔን እንደ አገዛዝ ማስወገድ የግድ ነውና ሊታለፍ የማ ይችል ግዳጅ ነው---ዴሞክራሲያዊና ለኢትዮጵያ የሚበጅ ሽግግር ከተፈለገ ፡፡

ይህን በተመለከተ ያለን ተጨባጭ ግምገማ የመለስ ሞት ከሕዝብ ትግል ድል አንፃር የሚሰጠው የረባ ጥቅም ከሌለ የሀገርና የሕዝብ ገዳዩ አረመኔ መሞት ከሚያሰኘን እሰይ ባሻገር ብዙ ማለት አንችልም የሚል ነው፡፡ የተከሰተውን ሁኔታ የሕዝብ ሀይሎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ ወይ ለሚለው አዎንታዊ መልስ መስጠት ዛሬ አይቻልም ፡፡ በርከት ያሉ ተቃዋሚ ነን ባይ ድርጅቶችና ቡድኖች ከቀሪዎቹ ወያኔዎች ለመደራደርና ለመ ተቃቀፍ ቋምጠው ጥሪ እየጠበቁ ወይም ባዕዳንን አስጠሩን እያሉ እየተማጠኑ ናቸው፡፡ ገና ብዙ ትግል አለ ብን ፡፡ በተጨባጭ በትግሉ ሜዳ በፀረ ወያኔ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንተባባር ለሚለው ጥሪ ማንም ምላሽ አ ልሰጠም ፡፡ በሀገር ወዳድ ድርጅቶች ላይ ዘመቻው ተጧጡፏል እንዲያውም በተፃራሪው፡፡ የፈሰሰው የሕዝብ ደም ፤ የተጨፈጨፉትና ደብዛቸው የጠፉ ዜጎች ፤ በየእስርቤቱና ማጎሪያው ፍዳ እየተቀበሉ ብዙ ሺ ዜጎች ፤ በደል የደረሰባቸው ምዕመናን ሁሉ ፤ በጋምቤላ ፤ በኦጋዴን ወዘተ የተፈጁ ዜጎች ፤ ክብራቸውንና መሬታ ቸውን የተነጠቁ ኢትዮጵያውያንና ለስደት የተዳረጉ ሁሉ ለመለስ ሞት አያለቅሱም ፡፡ ሰርጉን ተዝካር አይ ሉም ፡፡ አምባገነን ለምን ሞተ የሚል መገዛት የለመደ ውዳቂ ፍጡር ብቻ ነውና ፡፡ ለነገሩ መለስ ዜናዊ መ ሞት ከነበረበት ጊዜ ብዙ ብዙ ዓመታት አልፈዋል ፡፡ ሀዘን ቢሰማን ለሕዝብ ፍርድ ሳይቀርብ መሞቱ ብቻ ነ ው ፡፡ የአምባገነኑን ሞት ለወያኔ ቀውስ መባባስና ለውድቀቱ ለመጠቀም ሕዝብና የሕዝብ ድርጅቶች መዋ ደቅ መጣር አለብን/አለባቸው ፡፡ ወሳኝ አማራጭ ላይ ደርሰናል ፡፡ ነቃ ብለን የሀገር ማዳኑን ትግል እናጧጥ ፍ ፡፡

ሕዝባዊ አመፅ እውን ይሁን!
ፀረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም !
የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶቹን ሁሉ ያደባያል

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France